


# ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ

በሶዞፖሊስ ከተማ ከባለሥልጣን ቤተሰቦች ተወለደ አያቱም ስሙ ሳዊሮስ ይባላል የሶዞፖሊስ ከተማ ጳጳስ ነበር የ431ዱን የኤፌሶን ጉባኤ የተሳተፈ አባት ነው ፤ እንግዲህ ታናሹ ሳዊሮስ በኋላ ሕይወቱን በሙሉ የሚዋጋለት ኤፌሶን ገና ሳይወለድ በደሙ ነበር።

በ485 ወደ እስክንድርያ በመሔድ የግሪክ እና ላቲን ሰዋስው የንግግር ክህሎት (Rhetoric) ተማረ በዚህ ጊዜ ሳዊሮስ ገና የክርስትናን ጥምቀት ባይጠመቅም እስክንድርያ ታላቅ የኬልቄዶን ጉባኤ ተቃውሞ ማእከል ነበረችና በኋላ ላይ ለሚጠመቅመት ክርስትና ተጽእኖ ማድረጓ አልቀረም ፤ እንዲሁም ታላቆቹን የቀጳደቅያ አባቶች የተዋወቀው በዚህ እስንክድርያ ቆይታው ነው። የእስንክርያ ቆይታውን ካጠናቀቀ በኋላ ጠበቃ የመሆን አላማ ነበርውና ሕግ ይማር ዘንድ ወደ ቤይሩት አቀና። እንድጊድህ ይህ የሕግ ትምህርቱ ነበር በኋላ ላይ ኬልቄዶንን አንድ በአንድ የቃላትን ትርጉም እያወጣ ለመተቸት ያገዘው።

ሳዊሮስ በሶዞፖሊስ ታላቅ ጠበቃ የመሆን ሕልሙን ያመከነ አጋጣሚ ግን በቤይሩት አጋጠመው እርሱም ክርስቶስ ነበር! በጓደኛው ዘካርያስ ስኮላስቲከስ (በኋላ የሜልጢን ጳጳስ የሆነው) ክርስቶስን አገኘ ፤ የቤይሩት ተማሪዎች ብዙ ማጂክ እና አስማቶችን በሚለማመዱበት ወቅት እነርሱን በመቃወም የክርስቲያን ተማሪዎች movement በኤቫርጊዎስ የተመራ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ነበር ሳዊሮስም አስማቶቹን በመጥላት በጓደኛው በኩል ወደ

ክርስቲያን ተማሪዎቹ ጎን ቆመ ፤ ቀስ በቀስም ክርስትናን እና የትህርምት ሕይወትን ወደደ ከትምህርት ቤቱም አስማቶችን በማስወጣት ከክርስቲያን ተማሪዎቹ ቀንደኛ ሆነ። በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ ሳዊሮስ በኤቫርጊዎስ መሪነት በ488 በትሪፖሊ በቅድሱ ሌዎንቴዎስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የተጠመቀው።

ሳዊሮስ በዚህ ጊዜ ምንም አይነት የዓለማዊ ሕይወት ጉጉት ከውስጡ ወጥቶ ስለነበር ያለነውን ንብረት ሁሉ ለድሆች በማከፋፈል ወደ ኢየሩሳሌም ፓትሪአሪኬት በማምራት ማዩማ ፣ ጋዛ ውስጥ በሚገኘው የቅዱስ ሮማኖስ ገዳም ውስጥ የምንኩስና ሕይወትን ጀመረ። ሳዊሮስ ማንኛውም ሌላ ገዳም ቢመርጥ ኖሮ ሕይወቱ እንደ ሌሎች ገዳማውያን ክርስቲያኖች በሆነ ነበር "ንብረቱን ለድሆች በመስጠት ወደ ገዳም ገባ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜም እየተጋደለ ኖረ" በተባለለት ነበር ፤ የእግዚአብሔር መለኮታዊ መግቦት ግን ወደ ቅዱስ ሮማኖስ ገዳም መራው። በዚህ ጊዜ ኢየሩሳሌም አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ ነበረች ኬልቄዶናውያን እና ኢኬልቄዶናውያን እርስ በእርስ የሚጋጩባት ቦታ ነበረች ፤ የቅዱስ ሮማኖስ ገዳምም የኢኬልቄዶናውያን ማእከል ነበር። የኢየሩሳሌም ፓትሪአሪክ ግን ኬልቄዶናዊ በመሆኑ በንጉሥ ወታደሮች በመታገዝ ኢየሩሳሌምን ከኢኬልቄዶናውያን ለማጽዳት ሥራን እያጣጣፈው ስለነበር ወደ ቅዱስ ሮማኖስ ገዳምም ኔፋልዮስ የተባለውን መነክሴ ላከ በዚህ ጊዜ ነበር ሳዊሮስ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥብቅና ሚያፌዛቲዝም ጽሑፍ የጻፈው "Orationes ad Nephalium". በዚህ ጽሑፉ ሳዊሮስ ኬልቄዶናውያን  "2 Physis" እስካሉ ድረስ "2 Hypostasis" ማለት እንደሚጠበቅባቸው አለበለዚያ "1 Hypostasis , 2 Physis" ማለት ኢምክንያታዊ መሆኑን እና "Hypostasis" የሚለው ቃል በአባቶች ሁሉ "Concerete reality" እንደሚያሳይ በጥብቅ ሞገተ። ነገር ግን ኬልቂዶናውያኑ ሙግታቸው የሃሳብ ብቻ ሳይሆን የኃይል ነበርና ፤ በወታደሮች ኃይል ከገዳሙ አስወጧቸው። ቅዱስ ሳዊሮስም ከ200 መነኮሳት ጋር በመሆን ወደ ዋና ከተማዋ ቁስጥንጥንያ ለንጉሥ ለማመልከት በ508 አመራ።

የወቅቱ የቁስጥንጥንያ ንጉሥ አናስታሴዎስ ዳግማዊ ፤ ከእርሱ በፊት የነበረው ንጉሥ ዜኖ ያወጣውን ሄኖቲኮን ማስፈጸም የሚፈልግ ሰው ነበር (The Henotikon የሚለው document ሁለቱንም sides ለማስታረቅ የወጣ ነበር ግን ወደ ሁለቱም መንገድ መተርጎም በሁለቱም በኩል ላሉት extremes አጥጋቢ አልሆነም)። ነገር ግን የቁስጥንጥንያው ፓትሪአሪክ መቅዶንዮስ ኬልቄዶናዊ በመሆኑ ቅዱስ ቄርሎስ "የሁለት ባሕርይ" ደጋፊ ነው በማለት የኮቶች ጥርቅም (florilegium) ያዳርስ ነበር። ቅዱስ ሳዊሮስም ዝም አላለም ሌላ ሥራን አወጣ "the Philalethes" ፤ በዚህ ሥራውም ኬልቄዶናውያን ቄርሎስን ከአውድ ውጪ እየጠቀሱት እንደሆነና የቄርሎስ ባሕርያዊ ተዋሕዶ (Hypostatic Union) ትምህርት ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት ባሕርይን እንደማይፈቅድ ሞግቶ አሳየ። በዚህ ሥራውም መቅዶንዮስን በሚገባ ስለረታው ንጉሡ አናስታሴዎስ በሚያፌዚቲዝም አመነ ፤ ለተዋሕዶውያን ገዳማቸውን መለሰላቸው ፤ መቅዶንዮስን አስነሥቶ በቦታው ሚያፌዛይቱ ጢሞቴዎስ የቁስጥንጥያ ፓትሪአሪክ ሆነ ሳዊሮስም ዝናው በሁሉ ዘንድ ተሰማ ፤ በአሸናፊነትም ወደ ኢየሩሳሌም ገዳሙ በ511 ተመለሰ።

የሳዊሮስ አሸናፊነት በዚህ ብቻ አላበቃም በ512 ሶርያውያን በሲዶና ጉባኤ አድርገው ኬልቄዶናዊውን ፍላቪያኖስ አውርደው ሳዊሮስን የአንጾኪያ ፓትሪአሪክ አድርገው ሾሙት። ሳዊሮስ ታድያ እንደተሾመ ምን ቢያደርግ ጥሩ ነው? ኬልቄዶንን ፣ የልዮንን ጦማር ፣ ንስጥሮስን እና አውጣኪን በአንድ ላይ አውገዘ። እንዲሁም በ514 በጢሮስ ጉባኤ አድርጎ የዜኖ ሄኖቲኮን መተርጎም ያለበት በሚያፌዝትም እንደሆነና ኬልቄዶንንም "null

and void" እንዳደረገ አጸደቀ። እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ሚያፌዚትዝም firmly established ሆነ ነገር ግን ያለ ተቃውሞ አይደለም ሶርያ ፕሪማ በደስታ ብትቀበልም ፤ ግሪክ ተናጋሪዋ ሶርያ ሴኩንዳ ግን ኬልቄዶናውያን ነበሩ ነገር ግን የቁስጥንጥያ ንጉሥ ሚያፌዛይት በመሆኑ ምንም መፍጠር አልቻሉም ሳዊሮስ እና ቄርሎስ አሸንፈዋል ...

That is until the kings death. በ518 ንጉስ አናስታሴዎስ ሞተ ፤ በእርሱ ቦታም የላቲኑ ወታደር ዮስጢኖስ ንጉሥ ሆነ እርሱም ሮምን በማስደሰት እና Acacian Schism ከቁስጥንጥያ ጋር እንዲያበቃ ለመሥራት ቆርጦ ተነሣ ፤ ሮም ግን ለመታረቅ ያስቀመጠቸው ቅድመ ሁኔታ "ሳዊሮስ ይወገዝ ኬልቄዶን ይታወጅ" ነበር። (ዱሮውንም የችግሩ ፈጣሪ ሮም ፣ ጨራሿም ሮም ናት) ንጉሡም ሳዊሮስ እንዲታሠር እና ምላሱ እንዲቆረጥ ትእዛዝን አወጣ ነገር ግን ንግሥቲቱ ቴዎዶራ (የኋለኛው ንጉሥ Justinian ሚስት) ሚያፌዛይት ነበርችና (በቤተክርቲያናችን ቅድስት ናት) ለሳዊሮስ እንዲሸሽ አስጠነቀቀችው ፤ ቅዱስ ሳዊሮስንም እንደ ጌታ ሸሽቱን ወደ ግብጽ አደረገ ፤ የቅብጥ ቤተክርስቲያንም በደስታ ተቀበለችው እስካሁን በኬልቄዶን ያልተበገረች ቤተክርስቲያን በሮም ኢምፓየር ውስጥ እርሷ ነበርችና። ሳዊሮስም የቀረው ሕይወቱን 20 ዓመታት በስደተኝነት ከገዳም ወደ ገዳም ሲመላለስ ኖረ እንደ ጌታ እንኳን "የሚፈልጉህ ሞተዋልና ተመለስ" የሚለውን ቃል ለመስማት አልታደለም ነገሥታቱ ሶርያን በኃይለኛው ከተዋሕዶውያን እያጸዱ ነበርና በተለይ ጳጳሳቱን ሁሉ በማሰር ቄስ እና ዲያቆን ሚሾምላቸው በማጣት ይጠፋሉ በማለት አስበዋልና ፤ ጌታ ግን ቤተክርስቲያኑን አይተውምና ቅዱስ ያዕቆብ ዘእልበረዲን አስነስቶላታል ' ያዕቆብ በድብቅ እየተመላለሰ በየቦታው ጳጳሳት ፣ ካህናት ፣ ዲያቆናትን ይሾም ነበር የሶርያ ቤተክርስቲያንም ከእርሱ የተነሣ ስለቀጠለች እስካሁን ድረስ "ያዕቆባዊት" ትባላለች።

ሳዊሮስ ግን በግብጽ ስደት ውስጥም መጽሐፉን አላቆመም እስካሁን ታዋቂ የሆነውን ሥራውን "Contra grammaticum" የጻፈው በግብጽ ስደት ላይ ነው ፤ የዮሐንስ ግራማሪያንን እያንዳንዱን ሙግት አንድ ሳያስቀር ዶግ አመድ ያደረገበት ሥራው ነው። ይህንን ብቻ ሳይሆንንም ብዙህ መልክታትትን "defense to Justinian" የተባለውን ጽሑፍም የጻፈው በዚህ ጊዜ ነው። እውነት ለመናገር ከዚህ በላይ የኬልቄዶናውያንን ሙግቶች ማጥፋት ይችል ነበር ግን ከራሱ ከተዋሕዶአውያን መካከል ርጉሙ መናፍቅ ዮልያኖስ ፈረሳዊ (Julian of Halicarnassus) ተነሣ እንጂ ፤ ሳዊሮስም ከ528 እስከ 530 "Treatises against Julian of Halicarnassus" የተባሉ ብዙ ጽሑፎችን ጽፏል ርጉሙ ዮልያኖስ ባይነሣ ኖሮ ሳዊሮስ ኃይሉን ሙሉ በሙሉ ኬልቄዶናውያን ላይ ባደረገ ነበር። (ዛሬም የዮልያኖስን ምንፍቅና ለማስነሣት ሚሞክሩ ሰዎችን ሳይ የሳዊሮስ ትግል ትዝ እያለኝ እበግናለሁ)።

የሳዊሮስ ሙግቶች በኬልኬዶናውያን ዘንድ ባለመቻላቸው በኬልቄዶናውያን ዘንድ የእርሱን ሙግቶች ብቻ ለመመለስ "Neo-chalcedoniansim Movement" እስኪነሣ ነው የደረሰው ፤ ኬልቄዶናውያን ባይወዱትም የእነርሱን ነገረ ክርስቶስ ሳይቀር በጣም ነው influence ያደረገው ፤ ሳዊሮስ ማለት ብቻውን ኬልቄዶናውያን የንስሐ ዓለም አቀፍ ጉባኤ እንዲያካሒዱ ያደረጋቸው ሰው ነው (Constantinople II of 553 AD).

በመጨረሻም ቅዱስ ሳዊሮስ መልካሙን ገድል ተጋድሎ በየካቲት 15 ፣ 538 በሳካ ግብጽ ውስጥ አረፈ ከተጋድሎው የተነሣም "የሶርያውያን አክሊል" እየተባለ እስከዛሬ ድረስ ይወደሳል ምልጃውና በረከቱ ይደርብን።




"We remember... especially the chosen one of God, the Crown of the Syrians, the eloquent mouth, the pillar and doctor of the Holy Church of God as a whole, the meadow abounding in blossom, who preached all the time that Mary was undoubtedly the God-bearer**." the *Fifth Thubden* (Diptych) of the Syriac Liturgy**.